**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**
**Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity**
Efdpu@aol.com www.Finote.org

ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም.

## መግለጫ ከፍኖተ ዴሞክራሲ ዝግጅት ክፍል

በአገር ቤትና በጎረቤት አገሮች በሳተላይት የሚሰራጨው የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ራዲዮ ዝግጅት ትናንት ሐሙስ ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም. መቋረጡን ተረድተናል። ፕሮግራሙ የተቋረጠው ሳተላይቱና የሚያሰራጨው ኩባንያ (Nilesat) የተመዘገበት አገር (ግብጽ) መንግስት በኩባንያው ላይ ባደረገው ተጽእኖ መሆኑን መረጃ የደረሰን ሲሆን ተጽእኖ በምን ምክንያት ሊደረግ እንደቻለና ስርጭታችን ወደ ፊት በምን መልክ ሊቀጥል እንደሚችል የሚያብራራ ተጨማሪ መረጃ እንደደረሰን ለአድማጮቻችን እንገልጻለን። ወደ አገር ቤትና ጎረቤት አገሮች በሳተላይት አማካይነት የሚደረገው ስርጭት እስካሁን ስናሰራጭበት በነበረውም ሆነ በሌሎች አማራጮች መንገዶች እስክናመቻች ድረስ በየቀኑ ለ24 ሰዓት የምናስተላልፈውን ፕሮግራም በመላው ዓለም ለሚገኙ አድማጮቻችን በኢንተርኔትና በስልክ በቀጥታ ማስተላለፋችንን የምንቀጥል መሆኑን ለአድማጮቻችን በአክብሮት እንገልጻለን።

የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

ዝግጅት ክፍል